የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

Septemeber 03, 2026
Addis Ababa, Ethiopia

## PUBLIC NOTICE

## WARNING TO THE PUBLIC: FRAUDULENT EMAIL FALSELY PURPORTING TO BE FROM ECMA'S HUMAN RESOURCE DEPARTMENT, AND UNAUTHORISED USE OF ECMA ONLINE INVESTOR EDUCATION PARTICIPANT CONTACTS

This Notice is issued in the exercise of the Authority's Investor-Protection Objective Under Art. 5(1) of the Capital Market Proclamation No. 1248/2021 and its powers under Art. 6(27) to review risks to investor protection and market integrity and Art. 6(30) to take acts incidental or conducive to the attainment of its objectives.

Accordingly, the Authority has become aware that emails are being circulated to members of the public, including individuals who previously registered for or attended ECMA's online investor education sessions, which falsely use ECMA's name or otherwise seek to associate themselves with ECMA without the Authority's knowledge, involvement, or authorisation. The Authority is issuing this Public Notice to warn the public, to disclaim these communications, and to advise recipients on the steps they should take.

**1. Fraudulent Email Falsely Claiming to Be from ECMA's "Human Resource Team"**

An email has been circulated to a large number of recipients, sent from the address "ethcapitalmarketauthority@gmail.com" and using the display name "Ethiopian Capital Market Authority," with the subject line "Dear participants, Human Resource Team started hiring the best candidates." The email claims that ECMA's "Programme Coordination Team" and "Human Resource Team" have begun hiring recipients as staff, and asks recipients to send their full resume and qualification documents, in PDF format, to that email address by 10 September 2026.

THIS EMAIL DID NOT ORIGINATE FROM, AND IS NOT AUTHORISED, ENDORSED, OR RECOGNISED BY, THE ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY. The Authority confirms the following:

- ECMA does not use, and has never used, the email address "ethcapitalmarketauthority@gmail.com," or any other free/public email service (such as Gmail), to conduct official Authority business, including recruitment. All official ECMA correspondence is issued from the Authority's official domain, @ecma.gov.et.

- ECMA does not recruit staff, or request curricula vitae or personal documents from members of the public, through unsolicited mass emails. All genuine ECMA vacancy announcements are published through the Authority's official website and other verified official channels, and follow the Authority's standard, competitive recruitment procedures.

- Members of the public who have received this or a similar email are strongly advised not to reply to it, not to send any resume, national identification, financial information, or other personal document to the sender, and not to click on any link or open any attachment contained in it.

- Anyone who has already responded to this email or provided personal information in response to it is advised to cease further communication with the sender immediately and to notify the Authority using the contact details attached below.

This matter is being treated as a serious impersonation of the Authority and is under active investigation.

**2. Unauthorised Use of ECMA Investor Education Contacts for an Unrelated Solicitation**

The Authority has also become aware that individuals who registered for or attended an ECMA online investor education session have separately received an unrelated email, from a different sender, with the subject line "Invitation: Become a Founding Member of a New National SACCO," inviting recipients to become founding members of a proposed new savings and credit cooperative, and referring to the recipient's and sender's shared attendance at an ECMA investor education session.

The Authority wishes to make the following clear:

- ECMA has no affiliation with, and has not reviewed, vetted, approved, endorsed, or sponsored, the initiative referred to in that email, or its organiser.
- ECMA does not share, sell, or otherwise provide the contact details of investor education participants to any third party for solicitation or recruitment purposes of any kind. The Authority is separately investigating how its investor education participant contacts came to be used in this manner.
- The fact that an email references, or that its sender may have attended, an ECMA investor education session does not mean that ECMA endorses, supervises, or is in any way responsible for the initiative, organisation, or individual referring to it.

The public is advised to exercise ordinary caution before responding to this or any similar unsolicited email, and, in particular, before providing personal information or making any financial contribution: independently verify the identity, registration status, and legitimate purpose of any organisation before engaging with it, regardless of any reference the communication makes to ECMA or any ECMA event.

**3. General Guidance and How to Verify or Report**

To verify whether any communication genuinely originates from ECMA, or to report a suspicious email of the kind described in this Notice, the public may contact the Authority through the following official channels only:

- **Official website: www.ecma.gov.et**

- **Official email domain: any communication genuinely from ECMA will be sent from an address ending in @ecma.gov.et**

- **Investigation and Enforcement Department: +251 11 557 6123 or compliants@ecma.gov.et**

The Authority takes the protection of the public, and the integrity of its name and its investor education programmes, seriously, and will continue to monitor for, and take appropriate action against, any further misuse of the Authority's name or identity.

## ለህዝብ የተሰጠ አስቸኳይ የጥንቃቄ መልዕክት

## ከኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን የሰው ሃብት ስራ ክፍል የተላከ በማስመሰል የተሰራጨ ሐሰተኛ ኢሜይል፣ እንዲሁም ያለፈቃድ ጥቅም ላይ ስለዋሉ የኦንላይን ኢንቨስተር ትምህርት ተሳታፊዎች ኢሜል አድራሻ

ይህ ማሳሰቢያ በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2021 አንቀጽ 5(1) ስር በተደነገገው የባለስልጣኑ የኢንቨስተር ጥበቃ ዓላማ መሠረት፣ እንዲሁም ባለስልጣኑ ለኢንቨስተር ጥበቃ እና ለገበያ ተዓማኒነት የሚያሰጉ ሁኔታዎችን ለመገምገም በአንቀጽ 6(27) የተሰጠውን ስልጣን፣ እና ዓላማውን ለማሳካት አስፈላጊ ወይም አጋዥ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን በአንቀጽ 6(30) የተሰጠውን ስልጣን በመጠቀም የወጣ ነው።

በዚህም መሠረት፣ ቀደም ሲል በባለስልጣኑ ኦላይን ኢንቨስተር ትምህርት መርሃ ግብሮች ለተመዘገቡ ወይም ለተሳተፉ ግለሰቦችን እንዲሁም ለብዙ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የባለስልጣኑን ስም በሐሰት የሚጠቀሙ ወይም ያለ ባለስልጣኑ እውቅና፣ ተሳትፎ ወይም ፈቃድ ከባለስልጣኑ ጋር ግንኙነት እንዳላቸው አስመስለው የሚያቀርቡ ኢሜይሎች እየተሰራጩ መሆኑን ባለስልጣኑ ደርሶበታል። ባለስልጣኑ ይህንን ማስታወቂያ የሚያወጣው ህብረተሰቡን ለማስጠንቀቅ፣ እነዚህ መልዕክቶች ከባለስልጣኑ እንዳልመነጩ ለማሳወቅ፣ እና ይህ መልዕክት የደረሳቸው ግለሰቦች ሊወስዷቸው ስለሚገቡ እርምጃዎች ምክር ለመስጠት ነው።

### 1. ከኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን "የሰው ሃብት ቡድን" የተላከ በማስመሰል የሚሰራጭ ሃሰተኛ ኢሜይል

«ethcapitalmarketauthority@gmail.com» ከሚለው የኢሜይል አድራሻ የተላከ እና "Ethiopian Capital Market Authority" የሚለውን የመለያ ስም (Display Name) በመጠቀም "Dear participants, Human Resource Team started hiring the best candidates" የሚል ርዕስ ያለው ኢሜይል ለብዙ ግለሰቦች ተሰራጭቷል። ኢሜይሉ የባለሥልጣኑ "የፕሮግራም ማስተባበሪያ ቡድን" እና "የሰው ሃብት ቡድን" ኢሜል መልዕክሩን ተቀባይ የሆኑትን እንደ ሠራተኛ መቅጠር ጀመረ መባሉን ገልጾ፣ ሙሉ የሥራ ልምድ (Resume) እና የብቃት ማረጋገጫ ሰነዶቻቸውን በፒዲኤፍ (PDF) እስከ እ.ኤ.አ መስከረም 10 ቀን 2026 ዓ.ም. ድረስ ወደዚያው የኢሜይል አድራሻ እንዲልኩ ይጠይቃል።

ይህ ኢሜይል ከኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን የተላከ አይደለም፤ በባለሥልጣኑም እውቅና፣ ፈቃድ ወይም ድጋፍ የተሰጠው አይደለም።
ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ነጥቦች ያረጋግጣል፡

· ኦፊሴላዊ የባለሥልጣን ሥራዎችን (ቅጥርን ጨምሮ) ለማከናወን «ethcapitalmarketauthority@gmail.com» የሚለውን ወይም ሌላ ማንኛውንም ነጻ/የህዝብ ኢሜይል አገልግሎት (እንደ ጂሜይል ያሉ) ተጠቅሞ አያውቅም፤ አሁንም አይጠቀምም። ሁሉም ኦፊሴላዊ የባለሥልጣኑ ደብዳቤዎች የሚጻፉት ከባለሥልጣኑ ኦፊሴላዊ የድር አድራሻ @ecma.gov.et ነው።

· ባለሥልጣኑ በጅምላ በሚላኩ ኢሜይሎች አማካኝነት ሰዎችን አይቀጥርም፤ ከሕዝብ አባላትም የሥራ ልምድ ወይም የግል ሰነዶችን አይቀበልም። ሁሉም ትክክለኛ የሥራ ማስታወቂያዎች የሚታተሙት በባለሥልጣኑ ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ እና በሌሎች የተረጋገጡ ኦፊሴላዊ ቻናሎች በኩል ብቻ ሲሆን፣ ባለሥልጣኑ መደበኛ የውድድር ቅጥር ስርዓትን ይከተላል።

· ይህንን ወይም ተመሳሳይ ኢሜይል የደረሳቹ የህብረተሰቡ አካላት መልስ እንዳትሰጡ፣ ምንም አይነት የሥራ ልምድ፣ የብሔራዊ መታወቂያ፣ የፋይናንስ መረጃ ወይም ሌላ የግል ሰነድ ለላኪው እንዳትልኩ፣ እንዲሁም በውስጡ የሚገኙትን ማናቸውንም ሊንኮች ወይም አባሪዎች እንዳትከፍቱ በጥብቅ ይመከራል።

· ቀደም ሲል ለዚህ ኢሜይል ምላሽ የሰጡ ወይም የግል መረጃ ያቀረቡ ማንኛውም ሰዎች ከላኪው ጋር ተጨማሪ ግንኙነት ወዲያውኑ እንዲያቋርጡ እና ከዚህ በታች በተጠቀሱት አድራሻዎች ባለስልጣኑን እንዲያሳውቁ ይመከራሉ።

ይህ ጉዳይ የባለስልጣኑን ስም አላግባብ የመጠቀም ከባድ ተግባር ተደርጎ እየታየ ሲሆን፣ አሁን ላይ ጥብቅ ማጣራት እየተደረገበት ነው።

**2. ያለፈቃድ ለተለየ ጥሪ ጥቅም ላይ ስለዋሉ የባለስልጣኑ ኦንላይን የኢንቨስተር ትምህርት ተሳታፊዎች ኢሜል አድራሻ**

ባለሥልጣኑ በተጨማሪም የባለስልጣኑ ኦንላይን የኢንቨስተር የትምህርት መድረክ ላይ የተመዘገቡ ወይም የተሳተፉ ግለሰቦች ከሌላ ላኪ "Invitation: Become a Founding Member of a New National SACCO" የሚል ርዕስ ያለው፣ የዚህ ኢሜል ተቀባዮች አዲስ የታቀደ የብድር እና ቁጠባ የህብረት ሥራ ማህበር (SACCO) መስራች አባላት እንዲሆኑ የሚጋብዝ እና ተቀባዩና ላኪው በጋራ በባለስልጣኑ የኢንቨስተር ትምህርት መድረክ ላይ መገኘታቸውን የሚጠቅስ የተላከ ኢሜይል በተናጠል መቀበላቸውን ደርሶበታል። ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ነጥቦች ግልጽ ማድረግ ይፈልጋል፡

· ባለሥልጣኑ በዚያ ኢሜይል ውስጥ ከተጠቀሰው አስተባባሪ ወይም መስራች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እና ቁርኝት የለውም፤ የገመገመው፣ ያጸደቀው፣ የደገፈው ወይም ስፖንሰር ያደረገው ነገርም የለም።

· ባለሥልጣኑ የኢንቨስተር ትምህርት ተሳታፊዎችን መረጃዎች ለማንኛውም ሶስተኛ ወገን ለግብይት ወይም ለቅጥር አገልግሎት አያጋራም፣ አይሸጥም፣ ወይም በሌላ መልኩ አያስረክብም። ባለሥልጣኑ የኢንቨስተር ትምህርት ተሳታፊዎች አድራሻዎች በዚህ መልኩ እንዴት ጥቅም ላይ ሊውሉ እንደቻሉ በተናጠል እያጣራ ይገኛል።

· አንድ ኢሜይል የባለስልጣኑን የኢንቨስተር የትምህርት መድረክ መጥቀሱ ወይም ላኪው መሳተፉ ባለሥልጣኑ ማህበሩን፣ ድርጅቱን ወይም ግለሰቡን እንደደገፈው፣ እንደሚቆጣጠረው ወይም ለሚመለከተው ተነሳሽነት በኃላፊነት እንደሚጠየቅ አያመለክትምም።

ህብረተሰቡ ለዚህ ወይም ለተመሳሳይ ያልተጠየቁ ኢሜይሎች ምላሽ ከመስጠቱ በፊት፣ በተለይም የግል መረጃ ከመስጠቱ ወይም የገንዘብ መዋጮ ከማድረጉ በፊት፣ መደበኛ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ይመከራል፡- ኢሜይሉ ባለስልጣኑን ወይም የባለስልጣኑን ማንኛውንም መርሃ ግብር ቢጠቅስም እንኳ፣ ከማንኛውም ድርጅት ጋር ከመተባበሩ በፊት የድርጅቱን ማንነት፣ የምዝገባ ሁኔታ እና ህጋዊ ዓላማ ለብቻ ማረጋገጥ ይኖርበታል።

**3. አጠቃላይ መመሪያ እና እንዴት ማረጋገጥ ወይም ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል**

**ማንኛውም መልዕክት በእርግጠኝነት ከባለስልጣኑ የመጣ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ወይም በዚህ መልዕክት ላይ የተገለጸውን ዓይነት አጠራጣሪ ኢሜይል ሪፖርት ለማድረግ ሕዝቡ በሚከተሉት ኦፊሴላዊ ቻናሎች ብቻ ባለሥልጣኑን ማግኘት ይችላል።**
**· ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ: www.ecma.gov.et**

**· ኦፊሴላዊ የኢሜይል ጎራ (Domain)፡ ከባለስልጣኑ የሚላክ ማንኛውም ግንኙነት የሚያበቃው በ@ecma.gov.et አድራሻ ብቻ ይሆናል።**

**· የምርመራ እና አፈጻጸም ስራ ክፍል: +251 11 557 6123 ወይም compliants@ecma.gov.et**

ባለሥልጣኑ የህብረተሰቡን ደህንነት፣ እንዲሁም የስሙን እና የኢንቨስተር ትምህርት መርሃ-ግብሮቹን ተዓማኒነት በአግዝፎ የሚመለከት ሲሆን፣ የባለሥልጣኑን ስም ከዚህ በኋላ ለሚደረግ ማንኛውም አላግባብ እንቅስቃሴ መጠቀም ላይ ክትትል የሚያደርግና ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ የሚወስድ ይሆናል።